# አዳምን ባሰብኩ ጊዜ…

ፍሰሃ ጌትነት

(ቁም ነገር መጽሔት ቅጽ 13 ቁጥር 185 ነሐሴ 2006)

አዳምን የተዋወኩት ማህሌት በተሰኘችው የአጭር ልቦለዶች ስብስቡ ነው፡፡ ይሄው ከዚያ ጊዜ አንስቶ በሱ ስራዎች ተለክፌ ጸበል እንኳ የማይመልሰኝ አዳማዊ ሆኛለሁ፡፡ እኔ ቀድሜ ከአዳም ረታ ስራዎች ማህሌትን ላንብብ እንጅ የሱ የመጀመሪያ ስራ ግን እሷ አይደለችም፡፡ ከዚያ ቀደም ብሎ በ1970ዎቹ መጨረሻ ለአንባቢያን በወጣው ‹አባ ደፋር› የተሰኘ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱና በአጻጻፋቸው በዘመኑ ከነበሩት ደራሲያን የተለዩ ልቦለዶች ቦታ አግኝተውለታል፡፡ ከርዕሳቸው ጀምረው የተለዩ ናቸው፡፡ ‹ሲሮኮ›፣ ‹ሲፊኒክስ›፣ ‹እብዱ ሺበሺ› እና ‹ድብድብ› ይባላሉ፡፡

በማህሌት መጽሀፉ ውስጥ አዳማችን ያካተታቸው አጭርና ለኖቬላ የቀረቡ ልቦለዶቹ ደጋግመው የሚነበቡ ነበሩ፡፡ የደራሲውን ሰማይ ጠቀስ ችሎታ በደንብ የተመለከትኩበት መጽሐፉ ግን በሻማ ቡክስ የታተመው ‹‹ግራጫ ቃጭሎች›› የተሰኘው ረጅም ልቦለዱ ነው፡፡ በዘመኔ የነበሩ አንባቢዎች የአዳምን ጽሁፎች ‹የማይገቡና ግራ የሚያጋቡ› እያሉ ሲገልጽዋቸው እሰማ ነበር፡፡ እኔን ግራ የሚያጋቡኝ ግን የአዳም ልቦለዶች ሳይሆኑ የአዳም አንባቢዎች ነበሩ፡፡ ለምን ግራ እየተጋቡ ደጋግመው ያነቡታል፡፡ እኔ እነሱን ብሆን ፊቴን አዙሬ ሌላ ደራሲ እፈልጋለሁ እንጅ ችክ አልልም ነበር፡፡ ሌሎች የእኔ ሽርክ የሆኑ አንባቢዎች ደግሞ የአዳምን ልቦለዶች በተለየ መንገድ ይገልጽዋቸዋል፡፡ ‹‹ ደጋግሞ ቢነበብ የማይሰለች፣ ቀስ እያለ ቆዳን አልፎ ከልብ የሚስማማ›› በሚል አረፍተ ነገር፡፡

በአጫጭር ልቦለዶቹና በ‹ደርሶ መልስ› ረዥም ልቦለዱ (እነዛጎልም ሳይረሱ) መጽሐፉ ያስደሰተኝ እንዳለጌታ ከበደ ደግሞ አዳምን በዚህ መንገድ ገልጾት አንብቤ እንደገና ደስ ብሎኛል፡-

‹‹በእኔ ንባብ፤ በአማርኛ በአጫጭር ትረካዎች ዘርፍ እንደ አዳም ረታ ‹‹ብዙ ነገር›› የሰጠን የለም፡፡ ‹‹ብዙ ነገር›› ስንል በቁጥር ብዛት ብቻ ሳይሆን በሀሳብ ጥራትም ጭምር ነው፡፡ ለቴክኒክ አወቃቀሩ፣ ለሀሳብ አከያየኑ አብዝቶ እንደሚጨነቅ ስራዎቹ ‹‹ዘብ ቆመው›› ይሟገቱለታል፡፡ አሮጌው መንገድ የሰለቸውና ብዙዎቹ ባልሄዱበት ወይም በአዲስ ጥርጊያ መንገድ ለመጓዝ ሁሌም ትጥቁን እንደጠበቀ ነው፡፡ ›› (ፋክት መጽሔት ቅጽ 2 ቁጥር 17 ጥቅምት 2006 ገጽ 20)

የአዳም ልቦለዶች ከተለመደው ቅርጽ የወጡ ናቸው፡፡ ከ ‹ሀ› ጀምረው እስከ ‹ፐ› የሚዘልቁ አይደሉም፡ ፡ ከ ‹ፈ› ጀምረው ወደ ‹ሀ› የሚመለሱ ከዚያ እንደገና ወደ ‹አ› የሚጓዙ ወ.ዘተ…. ናቸው፡፡ መነሻና መድረሻ ፍለጋ የአዳምን መጽሀፍ የገለጠ ተደራሲ ይከስራል፡፡

ዛሬ አዳም ትዝ ባለኝ ጊዜ (ሁሌም ትዝ እንደሚለኝ ሁሉ) በመጽሐፍቶቹ መካከል ተጋድሜ እሱን ማየት ፈለግኩ፡፡ የመጽሀፍቱን ገጽ እየገለጥን አብረን እንመለከተው ዘንድ ጋብዣችኋለሁ፡፡

**አዳም ስለ ሴቶች**

ይሄኛው አዳም እንደ መጀመሪያው አዳም አይደለም፡፡ ያኛው ሞኝ ነው፡፡ ከአንዲት ሄዋን ውጭ የማያውቅ፣ ከአንዲት ሴት በላይ የማያደንቅ፣ የተባለውን ሁሉ የሚያደርግ ጅላጅል ቢጤ ነው፡፡

ይሄኛው ግን ይለያል፡፡ ሴትን በአይነት በአይነቷ ይመድባታል፡፡ ከዳሽን ተራራ በላይ ሰቅሏት፣ ዳሎል ላይ ይፈጠፍጣታል፡፡ በአዳም ረታ ብዕር ሴት ልጅ ከፍ፣ ዝቅ ተደርጋ ተስላለች፡፡

በግራጫ ቃጭሎች ልቦለዱ ወሰንን ከነጨረቃነቷ፣ ከነማማሯ እጇን ይዞ ወደ ከፍታው ይወስዳታል፡፡ መዝገቡ ብቻ ሳይሆን እኛም ሳናስበው ከወሰን ጋር ፍቅር ይይዘን ዘንድ የማርያም መንገድ ይለቅልናል፡፡ ትርንጎንስ ብትሉ! ያች እንኳ በኖቬላዎቹ ውስጥ ደጋግሞ የሚያነሳት፡፡ ‹‹መች ትመጣለህ›› በሚለው ኖቬላው ውስጥ ለፋሲካ ዕለት ወንድ የምትቀጥረው ትርንጎም በአዳም ረታ የምትወደድ ተደርጋ ተስላለች፡፡ ወዲህ ደግሞ በጥንቅሽ ላይ ጨክኖባታል፡፡ ህማማትና በገና በሚለው መጽሀፉ ውስጥ ‹‹ስንዝሮ›› የተባለ አጭር ልቦለድ ተካቷል፡ ፡ ጥንቅሽን የምናገኛት እዚያ ነው፡፡ መሬት ላይ ጥሎ ሲደበድባት፡፡ እንዲህ ይገልጻታል፡- ‹‹ዘመናዊ የመሰለች፤ ግን ሲያልፍም ያልነካት፣ ከጨርቃ ጨርቅ፣ ከወሲብና ከአርቲ ቡርቲ ከምንትስ በተለየ ነገር ያልፈረጀች.. አንጎሏ ከቁራ ስጋ ያልተለየ… የኾነች ሻኛ፣ የሆነች ፍሪምባ…››

እንዲህ እንዳትሞት እንዳትድን አድርጎ ካረከሳት በኋላ ህቅታዋን ስንጠብቅ ዝቅ ብሎ በርህራሄው (ማንስ በሴት ይጨክናል) እስትንፋስ ይሰጣታል፡፡ ከሞት አፋፍ ይመልሳታል፡፡ እንዲህ በሚሉ ቃላት፡-

‹‹… ቢሆንም ጥንቅሽ ውብ ናት፣ ባልና ሚስት ተብሎ ገላዋን መሞቅና የምትወልዳቸውን ልጆች ማቀፍ… ቋንቋ ሊገልጸው የማይችለው ውበትና ደስታ ነው፡፡››

ይሄ አዳም እንደመጀመሪያው አዳም አይደለም፡፡ ሴት ያነሳል፤ ሴት ይጥላል፤ በሴት ይሞታል፤ ሴት ይገድላል፡ ፡

**አዳምና ገለጻው**

አሁን በሞቴ አሜሪካና ጠላ አብረው ይሄዳሉ? በአንድ አረፍተ ነገር ውስጥ ስማቸው እኩል ሊጠራ ይችላልን? አዳም ግን ይሄንን አድርጓል፡፡ በሚጣፍጥ አገላለጽ አሜሪካን ከጠላ ጋር ያወዳድራታል፤ ያወራርዳታልም ጭምር እንጅ! ‹ዓይን› በተሰኘው አጭር ልቦለድ ውስጥ ጠላ የሚወደው አንድ ገጸ ባህሪይ እንዲህ ይለናል፡

- ‹‹ሚሊዬን ብር ሠጥተው አሜሪካ ፍሎሪዳ አሁኑኑ በነጻ እንላክህ ቢሉኝ መጀመሪያ ጠላዬን ልጨርስ ነው የምላቸው››

ይሄን ባነበብኩበት ወቅት አሜሪካን እንዴት እንደናቅኳት አትጠይቁኝ፡፡ የአዳም አማርኛ ይጣፍጠኛል፡፡ እንደናና ከረሜላ፡፡ መዝገቡ (የግራጫ ቃጭሎቹ) እንደሚወደው፡ ፡ ስለ አንዲት ሴት የሚገልጸውን ትርክት አንብቡና ታዘቡኝ፡፡

‹‹እሷ ጠይም ናት፡፡ ቅላት የተቀላቀለበት ጠይም፡፡ ከንፈሮቿ ጢቅ ያሉ…. ሊፈነዱ የደረሡ ናቸው፡፡ ባትስቅም ጉንጮቿ ላይ ደብዘዝ ብሎ የሚታይ ብትፍለቀለቅ በድምቀት የሚሠረጉድ ረባዳ አለ፡፡ አፍንጫዋ

ቀጥ ብሎ ወርዶ ጫፍ ላይ ሲደርስ ለአመል ቀና ይላል፡፡ አይኖቿ ትልልቅና መውጣት የፈለጉ የሚመስሉ ናቸው፡፡ አስተያየቷ ውስጥ ፈገግታ፣ የዋህነት፣ አትንኩኝ ነገር…. እያየሽኝ ሙት… ጨካኝ ቆንጆ ነኝ… የሚነበብበት አይነት ነው፡፡ ሱዳሱድ ቅንድቦቿ ጢም ያሉ ናቸው፡፡ ግንባሯ ሰፋ ያለ ቸርነት የሚጋብዝ ነው፡ ፡ የሚሳም ግንባር ነው፡፡ የሚነካ ግንባር ነው፡፡ የወርቅ መስቀል፣ የአልማዝ መስቀል፣ ሜሮን የተነሰነሰበት መቅደስ … ብቻ መሳም እንደሚገባው ነው፡፡ ከፊሉ ግንባሯ ላይ ደግሞ እየተጠቀለለ የሚያንፀባርቅ ፀጉሯ፡፡ የኑግ ፈትል የሚመስል ፀጉርዋ… ቀሚሿ ቀይ ነው፡፡ ስስ ነውም መሰል የሁለቱን ጭኖቿን ቅርጽ አውጥቶአቸዋል፡ ፡ ይስባሉ፡፡ ጫማዋ ነጭ ነው፡፡ እግሯ የተወለወለ ምሽት ይመስላል፡፡ ቅጥነቱም በልክ ነው፡ ፡ … የጫማዋ ነጭ ቀለም ከሸሚዟ የዘነበ ይመስላል ›› (ህማማትና በገና ገጽ 97-98)

የአዳም ረታ የቋንቋ አጠቃቀምና አመራረጥ አንባቢውን ከገፀ ባህርያቱ ጋር እንዲግባባ ያደርገዋል፡ ፡ አንባቢው ከገፀ ባህርያቱ ጋር ያወራል፡፡ ይጫወታል፡ ፡ ይኮሳተራል፣ ይስቃል፤ ያዝናል፤ ይደሰታል፡፡ ብሎም ከገፀ ባህርያቱ ጋር በፍቅር ይወድቃል፡፡ ደራሲውን ዘንግቶ (ወይም ሙሉ ለሙሉ ረስቶ) ‹‹ምን አልክ?›› እያለ አንባቢው ከገፀ ባህርያቱ ጋር ወግ ይሰልቃል፡፡

እነሆ ሌላም የገፀ ባህሪ ገለጻ፡- ‹‹ፊቱ ሞጣጣ፣ ጥርሱ ፍንጭት፣ ከንፈሮቹ የሰለሉ፣ አንገቱ ረጅም፣ ግንባሩና አፉ ሠፊ፣ አፍንጫው የተዝለገለገ የመሰለ፣ ዐይኖቹ ትናንሽ፣ ትከሻው እንደጣውላ የተዘረጋና ድምፁ ወፍራም፣ ቁመቱ ከመርዘሙ የተነሳ እንደ አላማ ሰንደቅ ከሩቅ የሚታይ ነው፡፡ ብርሃኑ ይባላል ስሙ፡፡ አንድ ቃል ለመናገር አስር ጊዜ ሠማይ፣ አስር ጊዜ መሬት፣ አስር ጊዜ ግድግዳ፣ አስር ጊዜ የአድማጮቹን ፊት ያያል፡፡›› (ህማማትና በገና ገጽ 117)

**አዳምና ለዛው**

የአዳም ልቦለዶች ከማመራመር በተጨማሪ ለልባችን ሃሴት የሚፈጥሩና በድንገተኛ ሳቅ የሚያፈነዱም ናቸው፡ ፡ በግራጫ ቃጭሎች መጽሐፉ ውስጥ የተዋወቅነውና ከአዳም ረታ ምናባዊ ገፀ ባህርት መካከል አይረሴ የሆነው የነፋስ መውጫው መዝገቡ ጥርስ የማያስከድን ገፀ ባህሪ ነው፡፡ ህይወቱ ቢያሳዝነንም የሚነግረን ግን በሳቅ ሞልቶ ስለሚሆን የእሱን ሰቀቀን ረስተን ዘና እንላለን፡፡ ለምሳሌ ወሰን ስለምትባል ቆንጆዬ የሰፈሩ ልጃገረድ እንዲህ ያስባል( መቼም ወሰንን ሲወዳት ለጉድ ነው)፡- ‹‹ ብትስመኝ ምን ይጎልባታል? ጉንጬ ላይ በሚያምሩ ከንፈሮቿ ብትስመኝ… መሬት ይንቀጠቀጣል? ዓለም ይናወጣል? ትሞታለችን? ከብቶች ወተት መስጠት ያቆማሉ? እህል ማብቀል ያቆማል? ፀሀይ ደም ትመስላለች? አልነበረም›› ይላል፡፡ (ግራጫ ቃጭሎች ገጽ 99) ሌላ ጊዜ ደግሞ ከእንጀራ እናቱ ጋር ሲነጋገሩ ድንገት ከአንደበቱ ስለወጣው ሃሳብና ራሱን ስለተመለከተበት ደርዝ ይነግረናል፡-

‹‹አንድ ዕለት እንጀራ እናቴ በጠዋት አቡከታ ያስቀመጠችውን ሊጥ ውሻ ስለደፋባት እውጭ እየተንጐራደደች የኢትዮጵያን ውሾች ጠቅላላ ስትራገም አገኘሁዋት::

“ምን ታየኛለህ አንተ ደሞ ከውሻ አታንስም” አለችኝ::

“ሕይወት ወጣ ገባ ነው” አልኳት::

የሚረሳ አይደለም :: ሕይወት ወጣ ገባ ነው:: ፓፓ .. ፈላስፋ ሆንኩ::

ደግሞ ሌላ ቀን እንዲህ ይላል፡-
‹‹ስለነፍሳት ሳይንስ ስንማር አስተማሪያችን ጋሽ ዳንኤል ትልቅ የዝንብ ስዕል ግድግዳ ላይ ለጥፎ በእንጨት እየጠቆመ ስለ አካሏ ሲያወራን… ሲያስረዳን የሰማሁት ዝርዝር ተሰባስቦ ለጥቂት ሰኮንዶች ዝንቦች ሰው መሰል ፍጡራን መሰሉኝ፡፡ ከመሐል ገብቶን እንደሆነ ሊፈትሸን አስተማሪያችን መጠቆሚያ ዘንጉን ሲሰበስብ እጄን ወደ ላይ ሰቀልኩትና እንዲህ ብዬ ጠየቅኩት፡-

‹‹ጋሼ ዳንኤል ዝንቦች ያነጥሳሉ?›› ( ግራጫ ቃጭሎች ገጽ 59)

**የአዳም ልጆች**

አዳምን እዚህ ላይ ብንፎግረው ደስ ይለኛል፡፡ የአዳም ልጆች ሁሉን አውቃ ናቸው፡፡ የቻርለስ ዲከንስን ‹Great Expectation› መጽሀፍ ባነበብኩ ወቅት የተሰማኝ ስሜት የአዳምን ልቦለዶች ባነበብኩ ጊዜም ዳግም ይጎበኘኛል፡፡ የአዳም ልጆች እኛ አዋቂ ነን ባዮች የማናውቃቸውን ሁሉ ያውቃሉ፡፡ የምንወደው ትንሽ ልጅ መዝገቡ ዱባለ ግራጫ ቃጭሎች ላይ የሚለውን ለአብነት እንመልከት፡-

‹‹ጉብታዬ ከፈረሰ በሁዋላ ወደ ወንዝ እወርዳለሁ። ወደ ወንዝ የምወርደዉ የዋና ፍቅር ይዞኝ ሳይሆን ብዙ ራቁታቸዉን የሚታጠቡ ሴቶች ስለማይ ነበር። ገለል ያለ “ኮካ” መሬት መርጬ እቀመጥና አያለዉ። የብዙዎቹ ሴቶች ጡቶች ትላልቆች ናቸዉ። እነዚህ ጡተ ትላልቆች ሴቶች ለመታጠብ አያፍሩም፤ ጡቶቻቸዉን ሳሙና ቀብተዉ ግራና ቀኝ እያወናጨፉ ድንጋይ ላይ ተቀምጠው በፀሀይ እየተንቃቁ (ጋኔንም አይፈሩ?)። አንዳንዴም በመንገድ በልብስ የተሸፈነ የሴት ደረት አይና እዚያ ውስጥ ሊኖር የሚችለዉን የጡት አይነት፣የቆዳ ልስላሴ የመሳሰሉ ብልቶችን ውበት በሀሳቤ ልገምት እሞክራለዉ። አልችልም። ባለጌ ነኝ? ባለጌ ነበርኩእንዴ?››

ወይ መዝገቡ! እኔን አሳፈረኝ እኮ!

ለስንብት የአዳም ረታ ስራዎችን ዝርዝር ልንገራችሁ፡፡ ያነበባችኋቸው እንድትደግሟቸው በዚህኛው ጽንፍ ያላችሁ ደግሞ እንድትተዋወቋቸው እመክራችኋለሁ፡፡ (ምክር ገንዘብ አያስወጣምና)

ማህሌት(1981)
ግራጫ ቃጭሎች(1997)
አለንጋና ምስር (2001)
ከሰማይ የወረደ ፍርፍር (2002)
እቴ ሜቴ ሎሚ ሽታ(2002)
ይወስዳል መንገድ ያመጣል
መንገድ (2003)
ህማማትና በገና (2004)
ጭጋግና ጠል ፣ አባደፋርና ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች